http://www.ethcriminalawnetwork.com/

## የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን

"ሠርቶ አደሩ ሕዝብ...በሕገ መንግሥቱ ዝግጅት ቀጥተኛ ንቁና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ማድረጉ እጅግ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን የትግሉ ውጤቶች ዋናውና መብቱ ነው"

ጓድ መንግሥቱ ኃ/ማርያም
ነሐሴ 1977

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት

ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፑብሊክ ኢትዮጵያን እንመሠርታለን !

ከሕዝብ ውይይት በተገኙ አስተያየቶች መሠረት
ተሻሽሎ የተዘጋጀ

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# ሕገ መንግሥት

ረቂቅ 03

ነሐሴ 27 / 1978
አዲስ አበባ

ECLN

# ማውጫ


ገጽ

መቅድም .................................... 3

ክፍል አንድ

ሥርዓተ ማኅበር .................................... 6

ምዕራፍ አንድ፣ የፖለቲካ ሥርዓት .................... 6

ምዕራፍ ሁለት፣ የኢኮኖሚ ሥርዓት .................... 9

ምዕራፍ ሦስት፣ ማኅበራዊና የባህል ፖሊሲ .............. 11

ምዕራፍ አራት፣ አገርን መከላከል፣ ሕዝብንና አብዮትን መጠበቅ .............. 13

ምዕራፍ አምስት፣ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ .................. 14

ክፍል ሁለት

ዜግነት፣ ነፃነቶች፣ መብቶችና ግዴታዎች .................. 16

ምዕራፍ ስድስት፣ ዜግነት .......................... 16

ምዕራፍ ሰባት፣ የዜጎች መሠረታዊ ነፃነቶች፣ መብቶችና ግዴታዎች .............. 17

ክፍል ሦስት

የመንግሥት አወቃቀርና አሠራር .......................... 24

ምዕራፍ ስምንት፣ ቅርፀ መንግሥት .................. 24

ምዕራፍ ዘጠኝ፣ ብሔራዊ ሸንጎ .................... 24

ምዕራፍ ዐሥር፣ የመንግሥት ምክር ቤት ............ 30

ምዕራፍ ዐሥራ አንድ፣ የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ............ 32

ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ........... 35

ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት፣ የአስተዳደር አካባቢና የራስ ገዝ አካባቢ የሥልጣንና የአስተዳደር አካላት. 38

ምዕራፍ ዐሥራ አራት፣ ዳኝነት ...................... 40

ምዕራፍ ዐሥራ አምስት፣ የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት .......... 42


ECLN .../

## መቅድም

እኛ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ አሁን ከምንገኝበት ኋላ ቀርነት ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ለመሸጋገር የዘመናት አኩሪ ታሪካችንን መሠረት በማድረግ ፍትሕ፣ እኩልነትና ማኅበራዊ ብልጽግና የሰፈነበት ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ለመገንባት በከፍተኛ አብዮታዊ ትግል ላይ እንገኛለን::

ኢትዮጵያ የጥንት ገናና ሥልጣኔ ባለቤት የሆነችና ለብዙ ሺሕ ዓመታት ሳይቋረጥ የቆየ ነፃ መንግሥት ያላት አገር ናት::

የኢትዮጵያ መንግሥት [illegible]ጠወርታዊ ሆኖ የኖረ ነው:: የአገሪቱ ብሔረሰቦችና ልዩ ልዩ ማኅበረሰቦች በባህል መወራረስ፣ በፈለሳ፣ በንግድና በመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች፣ በሰላምና በጦርነት ጊዜ ተሳሰረው የኖሩ ናቸው:: ስለዚህ የኢትዮጵያ ረጅም የነፃነት ታሪክ የብሔረሰቦቿ የጋራ ሕልውናና የጋራ ትግል ታሪክ ነው::

ኢትዮጵያ የአፍሪካ፣ የእስያና የአውሮፓ አህጉሮች መገናኛ በሁነ ስትራቴጂያዊ አካባቢ የምትገኝ፣ የታላላቅ ወንዞች መነሻና ለም አገር በመሆኗ ባዕዳን በወረራ ሊይዟትና ሊከፋፈሉዋት ሞክረዋል:: በተለይም ካፒታሊዝም በምዕራብ አውሮፓ ካቆጠቆጠበት ከ16ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ ቅኝ ገዥዎች በቁጥጥራቸው ሥር ሊያደርጉት ተደጋጋሚ ሙከራ አድርገዋል:: ይሁን እንጂ ወራሪዎችና ቅኝ ገዥዎች በየዘመኑ የሰነዘሩትን ጥቃትና አገሪቱን ለመያዝ ያደረጉትን ሙከራ ሁሉ ሕዝቡ በቆራጥነት እየመከተ ድል ሲያደርግ ኖሯል:: ካፒታሊዝም ወደ ሞኖፖል ደረጃ በተሸጋገረበትና ኢምፔሪያሊስቶች ዓለምን ለመቀራመት በተነሳሱበት ወቅትም አልተበገረችም:: ይልቁንም በ1888 በጊዜው ዘመናዊ በነበረው የቅኝ ገዥ ጦር ላይ የተቀዳጀችው ታላቁ የዓድዋ ድል በዓለም ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ልዩ የነፃነት ተጋድሎን ክብርና አኩሪ ታሪክን አጎናጽፏታል:: [illegible]አርበኞቿ የአምስት ዓመታት ትግልና መስዋዕትነትም ፋሺዝምን ድል በመምታት ስታሪክ ተረጋግጦ የቆየውን የነፃነት አርማዋን ከማውለብለብ የሚገታት ኃይል አለመኖሩን እንደገና አስመስክራለች::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጠላት የሚሰነዝርበትን ጥቃት እየመከተና ተደጋጋሚ ድሎችን እየተቀዳጀ አልደፈር ባይነቱንና ለነፃነት ቀናኢነቱን እያረጋገጠ አገሩን አስከብሮ ኖሯል::

ECLN

.../

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ በዚህ የረጅም ዘመን ታሪኩ በልዩ ልዩ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች ውስጥ የተጓዘ ሲሆን በዚሁ ሂደት ላይ መራራ የመደብ ጭቆናና የብዝበዛ ጊዜ አሳልፏል:: በተለይም በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ የነበረው ግንኙነት ገበሬውን አስከፊ በሆነ የጭቆና ቀንበር ሥር ጥሎት እንደነበር ይታወቃል:: ፊውዳሎች በየጊዜው በመካከላቸው በሚያነሱት ግጭትና ጦርነትም ሕዝቡ ሲማገድ፣ የጉልበቱ ውጤት የሆነውን ምርት በልዩ ልዩ መንገድ ሲቀማ፣ ረሃብ፣ በሽታና እልቂት ሲፈራረቁበት ኖሯል::

ካፒታሊዝም ማቆጥቆጥ ጋር ደግሞ በሥርዓቱ ውስጥ ቅራኔው እየተካረረ መጥቶ ሕዝቡ ጭቆናውን ሊሸከመው ከማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ ተራማጅ የኅብረተሰቡ ክፍሎች በከፈሉት ከፍተኛ መሥዋዕትነት የፊውዳሉ ሥርዓት ሊገረሰስ ችሏል:: በዚህ መሠረት በ1966 የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አብዮታችን ለዛሬው ሕዝባዊ ልዕልና በር ሊከፍት በቅቷል::

አብዮቱ በተቀጣጠለበት ወቅት የተደራጀ ግንባር ቀደም አመራር ሰጪ አካል ስላልነበረ፣ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ወገን የሆነው የመለዮ ለባሹ ክፍል ትግሉን አስተባብሮ መምራት ጀመረ:: ከዚያም የዘውዱ አገዛዝን በማስወገድና በተከታታይ ልዩ ልዩ አብዮታዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ለአዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት መሠረት ጣለ:: የገጠር መሬት፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች፣ ታላላቅ የማምረቻ፣ የማከፋፈያና አገልግሎት ሰጭ ተቋሞች የሕዝብ ሀብት ሆነዋል:: ለብሔረሰብ፣ ለጾታና ለሃይማኖት እኩልነት ሁኔታዎች ተመቻችተዋል:: ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በየፈርጁ እየተደራጀ በአገሩ ጉዳይ ወሳኝ የሚሆንበት መብት ሊቀዳጅ ችሏል::

እኛ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ፍትሕ፣ እኩልነትና ብልጽግና የሰፈነበትን የአዲሱን ኅብረተሰብ ግንባታ ትግል በውል ለመያዝ የበቃነው በቀላሉ አይደለም:: የመደብ ጠላቶቻችን ከፊታችን የደቀኗቸውን ብርቱ ፈተናዎች መወጣት ቀዳሚ ተግባራችን ነበር:: ቀደምም ለነፃነታችንና ለአንድነታችን መከበር ስንዋደቅ እንደኖርን ሁሉ፣ ዛሬ ደግሞ "አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት" ብለን በመነሳት ለዓላማችን ግብ መምታት እየተፋለምን አሁን ለምንገኝበት ለፈጣን ማኅበራዊ እድገት አመቺ ወቅት ልንበቃ ችለናል::

ECLN

.../

በአሁኑ ጊዜ እኛ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ዋና ትኩረታችን ልማት ሲሆን፣ በአጠቃላይ ዓላማችንም ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን እያጠ ናቀቅን ለሶሻሊዝም ግንባታ ተፈላጊውን ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት መጣል ነው:: ይሁን እንጂ ፀረ አብዮትና ፀረ ሶሻሊዝም የሆኑ ኢምፔሪያሊስትና የአድኅሮት ኃይሎች ጠቀኛ የእድገት ጉዟችንን ለማደናቀፍ ከመሞከር ስለማይታቀቡ ይህን አደራጎታቸውን መቋቋም ሌላው የትግላችን ግንባር ነው::

እኛ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ የመራራ ትግላችን ውጤት የሆነውን የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲን አመራር የተቀዳጀን በመሆኑ፣ የፖለቲካ ባህላችንን እያዳበርን ዓላማችንን ከግብ ለማድረስ በምንችልበት አስተማማኝ ሁኔታ ላይ እንገኛለን:: በዚህ መሠረት የአባቶቻችንን አደራ ከማስከበር ጋር የአዲስ ሥርዓተ ማኅበር ግንባታን ታሪካዊ ተግባር በስፋት ተያይዘናል:: ጥረታችን ፍሬ እያስገኘ ለግባችን መብቃት እንችል ዘንድ የአዲሱ ፖለቲካ ሥርዓት መሟላት አስፈላጊ ሁኔታ ነው::

በዚህ መሠረት እኛ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ:—

- ሙሉ የሥልጣን ባለቤትነታችን የሚገለጽበትን፣
- የራሳችንን ዕድል በራሳችን በመወሰን የአገራችን አንድነትና የብሔረሰቦች እኩልነት የሚረጋገጥበትን፣
- መሠረታዊ ነፃነቶችና መብቶች የሚጠበቁበትንና ግዴታዎች የሚከበሩበትን፣
- ለሶሻሊዝም አስተማማኝ መሠረት የሚጣልበትንና የሚገነባበትን፣
- ለዓለም ሰላም፣ ለፍትሕ፣ ለዲሞክራሲና ለማኅበራዊ እድገት ተገቢ አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚያስችለውን፣

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚመሠረትበትንና የሚተዳደርበትን ይህን የአገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነውን ሕገ መንግሥት ከ ______________ እስከ ______________ 19__ ባደረገነው ውሳኔ ሕዝብ አጽድቀናል::

ECLN

..../

# ክፍል አንድ
# ሥርዓተ ማኅበር

## ምዕራፍ አንድ
## የፖለቲካ ሥርዓት

### አንቀጽ 1

1. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሠራተኛውና በገበሬው ኅብረት፤ በምሁሩ፣ በአብዮታዊ ሠራዊት፣ በዕደ ጥበብ ባለሙያውና በሌሎች ዲሞክራሲያዊ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ መንግሥት ነው::

2. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ደሴቶቹን ጨምሮ የየብስ፣ የአየርና የባህር ግዛቱ የማይነጣጠልና የማይደፈር ሉዓላዊ መንግሥት ነው::

3. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን እያጠናቀቀ ለሶሻሊዝም ግንባታ መሠረት ይጥላል::

### አንቀጽ 2

1. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሁሉም ብሔረሰቦች በእኩልነት የሚኖሩበት አሐዳዊ መንግሥት ነው::

2. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የብሔረሰቦችን እኩልነት ያስከብራል፤ ትምክሕተኝነትንና ጠባብነትን ይዋጋል፤ የሁሉንም ብሔረሰቦች ሠርቶ አደሮች አንድነት ያጠናክራል::

3. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በተለይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙት ትኩረት በማድረግ የብሔረሰቦችን ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ በደረጃ በማስተካከል የጋራ ብልጽግናቸውን ያረጋግጣል::

ECLN ..../

4. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአካባቢ የራስ በራስ አስተዳደርን ተግባራዊ ያደርጋል::

5. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የብሔረሰቦች ቋንቋዎች እኩልነትን፣ መዳበርንና መከበርን ያረጋግጣል::

## አንቀጽ 3

1. በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሥልጣን የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ነው::

2. ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነቱን ተግባራዊ የሚያደርገው በምርጫ በሚያቋቁማቸው ብሔራዊ ሸንጎና የአካባቢ ሸንጎዎች አማካይነት ነው:: የሌሎች የመንግሥት አካላት ሥልጣን ከነዚህ የመንግሥት ሥልጣን አካላት ይመነጫል::

3. ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ሥልጣኑን በውሳኔ ሕዝብም ተግባራዊ ያደርጋል::

## አንቀጽ 4

1. በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግሥት አካላት አደረጃጀትና አሠራር በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት መርሕ ላይ የተመሠረተ ነው::

2. ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት ሥልጣን አካላት በምርጫ ይቋቋማሉ:: የመንግሥት ሥልጣን አካላት ማእከላዊ አመራርንና የአካባቢ ሐሳብ አመንጪነትን በተግባር ያውላሉ:: የበላይ አካላት ውሳኔዎች በበታች አካላት ተፈጻሚ ይሆናሉ:: የበታች አካላት ለበላይ አካላት ተጠሪ ናቸው::

## አንቀጽ 5

የመንግሥት አካላት፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት፣ ባለሥልጣኖቻቸው፣ እንዲሁም ማንኛውም ግለሰብ ሶሻሊስት ሕጋዊነትን ያከብራሉ::

.../

## አንቀጽ 6

1. በማርክሲዝም ሌኒኒዝም የሚመራው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ለማገልገልና ጥቅሙንም ለማስከበር የቆመ ግንባር ቀደም ፓርቲ ነው።

2. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ የአገሪቱ የእድገት አቅጣጫ ቀያሽ፣ የመንግሥትና የመላው ኅብረተሰብ መሪ ኃይል ነው።

3. የፓርቲው አባላት ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትን ያከብራሉ።

## አንቀጽ 7

ሕዝባዊ ድርጅቶች በአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ ሕይወት ለሕዝብ ተሳትፎ መድረኮች ናቸው። በመንግሥት ፖሊሲ አወጣጥና አፈጻጸም ይሳተፋሉ።

## አንቀጽ 8

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት እድገት አቅጣጫ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በመንግሥትና ወሳኝ በሆኑ የኅብረተሰቡ ጉዳዮች ላይ ያለውን ተሳትፎ በማሳደግ፣ የመንግሥት አካላትን አደረጃጀትና አሠራር በማሻሻል፣ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ቁጥጥር በማጠናከር፣ የሕዝባዊ ድርጅቶችን ሚና በማዳበር፣ የመንግሥትንና የኅብረተሰቡን ተግባራት ሕጋዊ መሠረት በማጠናከር ለሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ መሠረት የመጣሉን ሂደት ማፋጠን ይሆናል።

.../

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

## ምዕራፍ ሁለት

## የኢኮኖሚ ሥርዓት

### አንቀጽ 9

1. መንግሥት የኢኮኖሚው ግንባታ መሠረታዊ ዓላማ የሆነውን የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የኑሮና የባህል እድገት ያዳብራል::

2. መንግሥት ሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን ደረጃ በደረጃ በማስፋፋትና በማጠናከር፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ የምርት ኃይሎችን እድገት በማፋጠን አገሪቱን ከኢኮኖሚ ኋላ ቀርነት ያላቅቃል::

3. መንግሥት ውስጣዊ ተደጋጋፊነትና ተዛምዶው ጠንካራ የሆነ ብሔራዊ ኢኮኖሚን ይገነባል፤ በገጠርና በከተማ፣ በጠረፍና በመሀል አገር ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነትም በጥብቅ ያስተሳስራል::

### አንቀጽ 10

1. መንግሥት የተፈጥሮ ሚዛን እንዲጠበቅ ያደርጋል፤ የተፈጥሮ ሀብት በተለይም መሬት፣ ውሃ፣ ደንና የዱር እንስሳ እንክብካቤ እንዲያገኝና እንዲዳብር በማድረግ ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጥቅም መዋሉን ያረጋግጣል::

2. መንግሥት ለልማት አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር የሕዝቡን አሠፋፈር ከተፈጥሮ ሀብት ሥርጭት ጋር እንዲመጣጠን ያደርጋል::

3. መንግሥት የገጠርን ኑሮ ከኋላ ቀርነት ለማላቀቅና ሕዝቡን ለተሻለ ማኅበራዊ ሕይወት ለማብቃት ተበታትኖ የሚኖረው ሕዝብ እንዲሰባሰብ ያበረታታል::

### አንቀጽ 11

መንግሥት የአገሪቱን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ በማእከላዊ ዕቅድ ይመራል::

ECLN

.../

## አንቀጽ 12

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የምርት መገልገያ ባለቤትነት ሶሻሊስት ማለትም የመንግሥት እና የኅብረት ሥራ ማኅበራት ባለቤትነት፣ የግል ባለቤትነትና በሕግ የሚወሰኑ ሌሎች የባለቤትነት ዓይነቶች ናቸው።

## አንቀጽ 13

1. የመንግሥት ባለቤትነት የሕዝብ ነው።

2. መንግሥት ቁልፍ የሆኑ የማምረቻ፣ የማከፋፈያና የአገልግሎት ድርጅቶችን በባለቤትነት በመያዝ በኢኮኖሚው መሪ ሚና ይኖረዋል። የተፈጥሮ ሀብት በተለይም መሬት፣ የማዕድን ሀብት፣ ውሀና ደን የመንግሥት ንብረት ነው። የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 14

መንግሥት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ባለቤትነት ሚና እያደገ እንዲሄድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ያበረታታል።

## አንቀጽ 15

የግል ባለቤትነት በመንግሥት ፖሊሲ እየተመራ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎችን እንዲያካሂዱ ይደረጋል። የግል ባለቤትነትን በሕግ መሠረት የማስተላለፍ መብት የተጠበቀ ነው።

## አንቀጽ 16

የግለሰብ ንብረት በሕግ የተጠበቀ ነው። የግለሰብ ንብረትን በሕግ መሠረት የማስተላለፍ መብት የተጠበቀ ነው።

.../

## አንቀጽ 17

መንግሥት ለኅብረተሰቡ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሕግ በሚወሰነው መሠረት ማንኛውንም ንብረት ሊገዛ፣ ተገቢውን ክፍያ በማድረግ ሊገለገልበት ወይም ካሣ በመክፈል ሊወርስ ይችላል።

## አንቀጽ 18

1. ሥራ የተከበረ የኅብረተሰቡ የሀብትና የደኅንነት ምንጭ ነው። የማንኛውም ሰው ማኅበራዊ አቋም የሚወሰነው በሥራው ነው።

2. መንግሥት "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው" የሚለውን መርሕ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ያደርጋል።

3. መንግሥት የኅብረተሰቡን ሥራ ወዳድነት፣ የሥራ ችሎታና ፈጠራ እንዲዳብር ያደርጋል።

## ምዕራፍ ሦስት

## ማኅበራዊና የባህል ፖሊሲ

## አንቀጽ 19

1. መንግሥት የዜጎችን የአእምሮና የአካል እድገትና የሥራ ብቃት በማዳበር አዲስ ባህልን ለመገንባትና ለሶሺያሊዝም መሠረት ለመጣል ትምህርትና ሌሎች የዕውቀት ማበልጸጊያ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል።

2. መንግሥትና ኅብረተሰብ ዜጎች የአካል ማሠልጠኛና ስፖርትን እንዲያዘወትሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ።

.../

## አንቀጽ 20

1. ቤተሰብ የኅብረተሰቡ መሠረት ስለሆነ መንግሥትና ኅብረተሰብ ልዩ ልዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶችንና ሌሎችንም ድጋፎች በመስጠት ይንከባከቡታል::

2. መንግሥትና ኅብረተሰብ ሕፃናት በሳይንሳዊ አስተሳሰብ ታንጸው፣ በሥነ ምግባር፣ በአእምሮና በአካል ጠንክረው፣ የአገር ፍቅር ያላቸውና ለሶሻሊዝም የቆሙ ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ ልዩ እንክብካቤ ያደርጋሉ::

## አንቀጽ 21

መንግሥትና ኅብረተሰብ የሕዝቡን ደኅንነት ለማሻሻል የጤና፣ የጡረታ፣ የመድንና የሌላም ማኅበራዊ ዋስትና አገልግሎቶችን ደረጃ በደረጃ ያስፋፋሉ::

## አንቀጽ 22

የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ሲያስከብሩና አብዮቱን ሲጠብቁ ጉዳት ለደረሰባቸው ታጋዮችና መሥዋዕት ለሆኑትም ታጋዮች ቤተሰቦች መንግሥትና ኅብረተሰብ ልዩ እንክብካቤ ያደርጋሉ::

## አንቀጽ 23

መንግሥትና ኅብረተሰብ የባህልና የታሪክ ቅርሶች እንዲጠበቁ፣ ጎጂ ልማዶች እንዲወገዱ፣ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በሶሻሊስት ሥነ ምግባር እንዲታነጽና ወዛደራዊ ባህል ደረጃ በደረጃ እንዲሰፋን ያደርጋሉ::

.../

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

## ምዕራፍ አራት

## አገርን መከላከል፣ ሕዝብንና አብዮትን መጠበቅ

### አንቀጽ 24

1. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሉዓላዊነቱንና የግዛት አንድነቱን ያስከብራል፤ አብዮቱንም ይጠብቃል።

2. የአገርን ሕልውናና አብዮትን መጠበቅ የመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ታሪካዊ ኃላፊነት ነው።

### አንቀጽ 25

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጽኑ የመከላከያ ኃይል ይኖረዋል።

### አንቀጽ 26

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመከላከያ ኃይል ለአገር አንድነትና ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ የበላይነት፣ ለሰላምና ለሶሺያሊዝም የቆመና የሚታገል የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ሠራዊት ነው።

### አንቀጽ 27

1. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአገሪቱን የመከላከል ችሎታ ያጠናክራል።

2. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የአርበኝነትና የአብዮታዊ ጀግንነት መንፈስ ያዳብራል፤ አገርን ለመከላከል፣ ሕዝብንና አብዮትን ለመጠበቅ እንዲሰለፍ ሳጊነቱ መላውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ያንቀሳቅሳል።

.../

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

3. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የወጣቱን ሶሻሊስት አርበኝነት ስሜት ያሳድጋል፤ የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎትንም በተግባር ያውላል::

4. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎችን ለመቋቋም ሲቪል መከላከያን ያደራጃል::

## ምዕራፍ አምስት
## የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ

### አንቀጽ 28

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የውጭ ፖሊሲ በወዛደራዊ ዓለምአቀፋዊነት፣ በሰላም አብሮ መኖርና በገለልተኝነት መርሆች ላይ የተመሠረተ ነው::

### አንቀጽ 29

1. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአገሪቱን ጥቅም በማስከበር ከሁሉም አገሮች ጋር በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነትንና ትብብርን ያዳብራል:: አገሮች በሚመርጡት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የመኖር መብታቸውን ያከብራል::

2. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ሁለገብ ግንኙነትንና ትብብርን ያዳብራል፤ ከዓለም አቀፍ የሠራተኛ መደብ ንቅናቄ፣ ከአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች፣ ከብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎችና ከሌሎች ዲሞክራሲያዊና ሰላም ወዳድ ኃይሎች ጋር ግንኙነቱን ያጠናክራል::

3. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢምፔሪያሊዝምን፣ ቀጥተኛና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን፣ ዘረኝነትንና ሌሎችንም የጭቆናና የብዝበዛ ገጽታዎች በጽኑ ይታገላል::

## አንቀጽ 30

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማይገሰሰው የአገሮች ብሔራዊ ሉዓላዊነትንና የግዛት አንድነትን፣ አንዱ በሌላው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባትን፣ አለመግባባቶችን በሰላም መፍታትን፣ ባጠቃላይም የገለልተኝነት መርሆችን መሠረት በማድረግ ለሕዝቦች መደጋገፍ፣ ለጋራ ልማትና ከጎረቤት አገሮች ጋር በመልካም ጉርብትና ላይ ለተመሠረተ ግንኙነት መጠናከር ጥረት ያደርጋል::

## አንቀጽ 31

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለሰው ልጅ ሰላም፣ ደኅንነትና እድገት በቁሙ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል::

.../

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

## ክፍል ሁለት

## ዜግነት፣ ነፃነቶች፣ መብቶችና ግዴታዎች

## ምዕራፍ ስድስት

## ዜግነት

### አንቀጽ 32

1. ማንኛውም ሰው ወላጆቹ ወይም ከወላጆቹ አንዱ ኢትዮጵያዊ ከሆኑ ኢትዮጵያዊ ነው::

2. ዜግነትን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች በሕግ ይወሰናሉ::

3. የውጭ አገር ዜጎችና ዜግነት የሌላቸው ግለሰቦች የኢትዮጵያን ዜግነት የሚያገኙበት ሁኔታና ሥርዓት በሕግ ይወሰናል::

### አንቀጽ 33

1. መንግሥት ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ የሚገኙትን ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም ያስከብራል::

2. መንግሥት አንድን ኢትዮጵያዊ ለሌላ መንግሥት አሳልፎ አይሰጥም::

### አንቀጽ 34

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለብሔራዊ አርነት፣ ለፀረ ዘረኝነት፣ ለሰላምና ለዲሞክራሲ በሚያደርጉት ትግል ምክንያት ጥቃት ለሚደርስባቸው የውጭ አገር ሰዎች ጥገኝነትን ይሰጣል::

.../

## አንቀጽ 35

1. በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ የሚገኙ የውጭ አገር ዜጎችና ዜግነት የሌላቸው ግለሰቦች በሕግ የተረጋገጡ ነፃነቶች፣ መብቶችና ግዴታዎች አሏቸው።

2. መንግሥት የውጭ አገር ዜጋንና ዜግነት የሌለው ግለሰብን በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት ካልሆነ በስተቀር ለሌላ መንግሥት አሳልፎ አይሰጥም።

## ምዕራፍ ሰባት

## የዜጎች መሠረታዊ ነፃነቶች፣ መብቶችና ግዴታዎች

## አንቀጽ 36

1. ኢትዮጵያውያን በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በሥራ ዓይነት፣ በማኅበራዊና በሌላም ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግባቸው በሕግ ፊት እኩል ናቸው።

2. የኢትዮጵያውያን እኩልነት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በባህል መስኮች ሁሉ በእኩልነት በመሳተፍ ይረጋገጣል።

## አንቀጽ 37

1. በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሴቶችና ወንዶች እኩል መብት አላቸው።

2. ሴቶች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በባህል መስኮች ከወንዶች ጋር በእኩልነት እንዲሳተፉ መንግሥት በተለይ በትምህርት፣ በሥልጠናና በሥራ ልዩ ድጋፍ ይሰጣል።

3. መንግሥት ለሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ጊዜ የጤና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው፣ ምቹ የሥራ ሁኔታ እንዲኖራቸውና በቂ የዕረፍት ጊዜ እንዲያገኙ ተገቢ እርምጃዎች ደረጃ በደረጃ እንዲወሰዱ ያደርጋል።

.../

## አንቀጽ 38

1. ጋብቻ ለአካለ መጠን በደረሱ በአንድ ሴትና በአንድ ወንድ መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው:: ባልና ሚስት በቤተሰብ ግንኙነታቸው እኩል መብት አላቸው:: ጋብቻ የመንግሥት ጥበቃ ይደረግለታል::

2. ልጆች በጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ ቢወለዱ እኩል መብት አላቸው::

## አንቀጽ 39

1. ኢትዮጵያውያን የመሥራት መብት አላቸው::

2. መንግሥት ብሔራዊ የኢኮኖሚ እድገትን መሠረት በማድረግ ደረጃ በደረጃ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ፣ የሥራ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ያደርጋል::

## አንቀጽ 40

1. የሠርቶ አደሩ የዕረፍት መብት የተጠበቀ ነው::

2. መንግሥት የሥራ ሰዓቶችንና የዕረፍት ጊዜያትን ይወስናል፤ ደረጃ በደረጃም ለሠርቶ አደሩ ዕረፍት የሚጠቅሙ ማኅበራዊ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል::

## አንቀጽ 41

1. ኢትዮጵያውያን ነፃ ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው::

2. መንግሥት ዕድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ ሕፃናት የግዴታ ትምህርት ደረጃ በደረጃ እንዲዳረስ ያደርጋል፤ በዓይነታቸውና በደረጃቸው የተለያዩ ትምህርት ቤቶችንና የሙያ ማሠልጠኛ ተቋሞችን ያስፋፋል::

.../

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

## አንቀጽ 42

1. ኢትዮጵያውያን በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂና በሥነጥበባት ምርምሮችንና የፈጠራ ሥራዎችን የማካሄድ ነፃነት አላቸው::

2. መንግሥት ዜጎች የሚያደርጉትን የምርምርና የፈጠራ ሥራዎች ያበረታታል፣ ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ኑሮ እድገትና ለሶሻሊዝም ግንባታ መፋጠን ለሚረዱ የምርምርና የፈጠራ ተግባራት ልዩ ድጋፍ ይሰጣል::

## አንቀጽ 43

1. ኢትዮጵያውያን የጤና እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው::

2. መንግሥት የጤና ተቋሞችን ደረጃ በደረጃ በማስፋፋት የጤና አገልግሎትን ይሰጣል::

## አንቀጽ 44

1. የኢትዮጵያውያን ሰብእና አለመደፈር የተረጋገጠ ነው::

2. የኢትዮጵያውያን መኖርያ ቤት አለመደፈር የተረጋገጠ ነው:: ሕግ ከሚደነግገው በስተቀር ማንም ሰው ያለ ባለቤቱ ፈቃድ ከሌላው ሰው መኖርያ ቤት መግባት አይችልም::

## አንቀጽ 45

1. ማንኛውም ሰው ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተገኘ ወይም በዐቃቤ ሕግ ትዕዛዝ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ካልሆነ ወይም ሕግ ከሚደነግገው በስተቀር አይያዝም::

2. ማንኛውም የተያዘ ሰው በ48 ሰዓት ውስጥ ወደ ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ወደ አቅራቢያው ፍርድ ቤት ለመድረስ የሚያስፈልገውን ጊዜ አይጨምርም::

## አንቀጽ 46

1. ማንኛውም ሕግን በመጣስ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በፍርድ ቤት ካልተወሰነበት በስተቀር ጥፋተኛ ሆኖ አይቆጠርም::

2. ተከሳሹን የሚረዳ ካልሆነ በስተቀር የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመ ልሶ አይሠራም::

3. ማንኛውም ተከሳሽ ራሱ የመከላከል ወይም የሕግ ጠበቃ የማቆም መብት አለው:: በከባድ ወንጀል ተከስ የሕግ ጠበቃ ለማቆም አለመቻሉ ለተረጋገጠለት ሰው በሕግ በሚወሰነው መሠረት መንግሥት በነፃ ያቆምለታል::

4. ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ ካልሆነ ወይም ሕግ ከሚደነግገው በስተቀር ሕጋዊ ምስክርነት የመስጠት ግዴታ አለበት፤ ሆኖም በኃይል ወይም በተፅዕኖ እንዲመሰክር አይገደድም:: በኃይል ወይም በተፅዕኖ የተገኘ ምስክርነት ሕጋዊነት አይኖረውም::

## አንቀጽ 47

1. የኢትዮጵያውያን የኅሊናና የሃይማኖት ነፃነት የተረጋገጠ ነው::

2. የሃይማኖት ነፃነት አጠቃቀም የአገርንና የአብዮትን ደኅንነት እንደዚሁም የሕዝብን መልካም ሥነ ምግባርና የሌላውን ዜጋ ነፃነት የሚነካ መሆን የለበትም::

3. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው:: የሃይማኖት ድርጅቶች ሕጋዊ አቋም በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 48

የኢትዮጵያውያን የንግግር፤ የጽሑፍ፤ የመሰብሰብ፤ ሰላማዊ ትዕይንተ ሕዝብ የማድረግና በማኅበር የመደራጀት ነፃነት የተረጋገጠ ነው::

.../

2. ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሥልጣኖችና ተቋሞች የቀረበውን አስተያየትና ሒስ መርምረው መልስ መስጠትና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል:: አስተያየትና ሒስ ባቀረበ ዜጋ ላይ የጥቃት እርምጃ መውሰድ በሕግ ያስቀጣል::

## አንቀጽ 53

ኢትዮጵያውያን በመንግሥት አካላትና በሕዝባዊ ድርጅቶች ወይም በባለሥልጣኖቻቸው ላይ አቤቱታ የማቅረብ መብት አላቸው:: የቀረበው አቤቱታ መመርመርና መልስ ማግኘት አለበት::

## አንቀጽ 54

1. የእናት አገርን ደኅንነት፣ አብዮቱንና የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ድሎች መጠበቅ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ታላቅ ክብር፣ ከፍተኛ ተግባርና ግዴታ ነው::

2. እናት አገርን መክዳት ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትል በሕዝብ ላይ የሚፈጸም እጅግ ከባድ ወንጀል ነው::

3. ብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት የማንኛውም ኢትዮጵያዊ መብትና ግዴታ ነው:: አፈፃፀሙ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 55

ኢትዮጵያውያን ሥራ ማኅበራዊ ጠቀሜታ ያለው የሰው ልጅ ሕይወት መሠረት መሆኑን በመረዳት፣ የሚሠራም በውጤቱ ተጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ፣ በየተሰማሩበት የሥራ መስክ ኃላፊነታቸውን የሥራ ዲሲፕሊንን አክብረው የንብረት እንክብካቤ በማድረግና ምርታማነታቸውን በማሳደግ የመሥራት ግዴታ አለባቸው::

..../

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

## አንቀጽ 56

1. ኢትዮጵያውያን ሶሻሊስት ንብረትን የመጠበቅና የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው።

2. መንግሥትና ኅብረተሰብ የታሪክ መዘክሮችንና የባህል ቅርሶችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ፣ ለማሰባሰብና ከጥቅም ላይ ለማዋል በሚያደርጉት ጥረት ኢትዮጵያውያን የመካፈል ግዴታ አለባቸው።

3. ኢትዮጵያውያን ተፈጥሮንና የተፈጥሮ ሀብትን በተለይም ደንን የማልማትና የአፈርና የውሃ ሀብትን የመጠበቅና የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው።

## አንቀጽ 57

ኢትዮጵያውያን የጾታና የሥራ ዓይነት እኩልነት እንዲከበር፣ በብሔረሰቦች ሠርቶ አደሮች መካከል መቀራረብ፣ መከባበርና ለሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ በጋራ የመሥራት ባህል እንዲሰፍን የማገዝ ግዴታ አለባቸው።

## አንቀጽ 58

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥትንና ሕጎችን ማክበርና የኢትዮጵያዊነትን ክብርና ሞገስ መጠበቅ ግዴታው ነው።

## አንቀጽ 59

የዜጎች ነፃነቶችና መብቶች አጠቃቀምና የግዴታዎች አከባበር በሕግ ይወሰናል። የዜጎች ነፃነቶችና መብቶች አጠቃቀም በሕግ ገደብ የሚደረግበት የመንግሥትና የኅብረተሰብ ጥቅም፣ እንደዚሁም የሌሎች ግለሰቦች ነፃነቶችና መብቶች እንዲከበሩ ብቻ ነው።

.../

ECLN

## ክፍል ሦስት

## የመንግሥት አወቃቀርና አሠራር

### ምዕራፍ ስምንት

### ቅርጸ መንግሥት

#### አንቀጽ 60

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በአስተዳደር አካባቢዎችና በራስ ገዝ አካባቢዎች የሚዋቀር አሐዳዊ መንግሥት ነው::

#### አንቀጽ 61

1. የአስተዳደር አካባቢዎች በተዋረድ ከከፍተኛ እስከ መሠረታዊ የሚገኙ የአስተዳደር አሐዶች ናቸው::

2. የአስተዳደር አካባቢዎች ክልል፣ ደረጃና ተጠሪነት በሕግ ይወሰናል::

#### አንቀጽ 62

1. የራስ ገዝ አካባቢዎች እንዳስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ የአስተዳደር አሐዶች ይኖሯቸዋል::

2. የራስ ገዝ አካባቢዎች ክልል፣ ደረጃና ተጠሪነት በሕግ ይወሰናል::

### ምዕራፍ ዘጠኝ

### ብሔራዊ ሸንጎ

#### አንቀጽ 63

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከፍተኛው የመንግሥት ሥልጣን አካል ብሔራዊ ሸንጎ ነው::

.../

ECLN


## አንቀጽ 64

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ሸንጎ በማንኛውም የአገር ጉዳይ ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ ሸንጎ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል:—

1. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን

ሀ. ሕገ መንግሥትና አዋጆች ያወጣል፤ ያሻሽላል፤ አፈጻጸማቸውንም ይቆጣጠራል፤

ለ. የውስጥና የውጭ ፖሊሲ ይወስናል፤

ሐ. የመከላከያና የደኅንነት ፖሊሲ ይወስናል፤

መ. የሰላምና የጦርነት ሁኔታ ይወስናል፤

ሠ. የአጭርና የረጅም ጊዜ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ እቅዶች ያጸድቃል፤

ረ. ዓመታዊ በጀት ያጸድቃል፤

ሰ. የገንዘብና የፋይናንስ ፖሊሲ ይወስናል::

2. የአስተዳደር አካባቢዎችንና ራስ ገዝ አካባቢዎችን

ሀ. ይመሠርታል፤ ክልላቸውን፤ ደረጃቸውንና ተጠሪነታቸውን ይወስናል፤

ለ. የሚተዳደሩበትን አዋጅ ያወጣል፤

ሐ. የገቢ ምንጫቸውን ይወስናል::

3. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን

ሀ. የመንግሥት ምክር ቤት፤

ለ. የሚኒስትሮች ምክር ቤት፤ ሚኒስትሮች፤ ኮሚሽነሮችና ባለሥልጣኖች፤

.../

ሐ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣

መ. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት፣

ሠ. ብሔራዊ የሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴ እና

ረ. የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት፣

ያቋቁማል::

4. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን

ሀ. ፕሬዚዳንት፣

ለ. ምክትል ፕሬዚዳንት፣

ሐ. የመንግሥት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ ፀሐፊና አባላት፣

መ. በአንቀጽ 87 ንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ መሠረት ሲቀርብለት ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮችና ሌሎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት፣

ሠ. በአንቀጽ 87 ንዑስ አንቀጽ 1/መ/ መሠረት ሲቀርብለት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶችና ዳኞች፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ የብሔራዊ ሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴ ሊቀመንበር እና ዋና ኦዲተር፣

ይመርጣል::

5. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በከፍተኛ የአገር ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሕዝብ እንዲሰጥባቸው ያደርጋል::

6. የአባላቱን የምርጫ ውጤት ትክክለኛነት ያረጋግጣል::

## አንቀጽ 65

ለብሔራዊ ሸንጎ አባልነት ዕጩዎች በኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አካላት፣ በሕዝባዊ ድርጅቶች፣ በወታደር ክፍሎችና በሌሎች በሕግ መብት በተሰጣቸው አካላት ይጠቆማሉ::

.../

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

## አንቀጽ 66

1. የብሔራዊ ሸንጎ አባላት ምርጫ የሕዝብን ብዛት መሠረት በማድረግ ሁሉ አቀፍ፣ እኩል፣ ርቱዕና በምሥጢር ይሆናል::

2. በምርጫው ሂደት ብሔረሰቦች በብሔራዊ ሸንጎ መወከላቸው ይረጋገጣል::

## አንቀጽ 67

የመረጠው ሕዝብ እምነት ያጣበትን የብሔራዊ ሸንጎ አባል ውክልና የመሠረዝ መብት አለው::

## አንቀጽ 68

ብሔራዊ ሸንጎ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል:: አስቸኳይ ስብሰባ በመንግሥት ምክር ቤት ወይም በሪፑብሊኩ ፕሬዚዳንት ውሳኔ ወይም ከአባላቱ ከሦስት አንዱ እጅ ሲጠይቅ ይጠራል::

## አንቀጽ 69

1. የብሔራዊ ሸንጎ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል::

2. የሸንጎው የሥራ ዘመን ከመፈጸሙ ሁለት ወር በፊት የአዲሱ ሸንጎ ጠቅላላ ምርጫ ይከናወናል:: የነባሩ ሸንጎ የሥራ ዘመን እንደተፈጸመ ያለው የመንግሥት ምክር ቤት አዲሱን ሸንጎ ይጠራል::

3. አዲሱ ሸንጎ እንደተሰበሰበ የመጀመሪያ ተግባሩ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን የመንግሥት አካላት አባላት መምረጥ ይሆናል::

4. አዲስ የተመረጠው ሸንጎ ተሰብስቦ የመንግሥት ምክር ቤትንና የሪፑብሊኩን ፕሬዚዳንት እስከሚመርጥበት ጊዜ ድረስ ያለው የመንግሥት ምክር ቤትና ያለው ፕሬዚዳንት በሥልጣን ላይ ይቆያሉ::

## አንቀጽ 70

በጦርነት ጊዜ ወይም ሌላ አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥም ብሔራዊ ሸንጎ ሁኔታው እስከሚወገድበት ጊዜ ድረስ የሥራ ዘመኑን ሊያራዝም ይችላል::

## አንቀጽ 71

ብሔራዊ ሸንጎ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚሽኖችን ያቋቁማል::

## አንቀጽ 72

የመንግሥት ምክር ቤት፣ የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት፣ የብሔራዊ ሸንጎ ኮሚሽኖች፣ የብሔራዊ ሸንጎ አባላት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ ከፍተኛ የአስተዳደር አካባቢና የራስ ገዝ አካባቢ ሸንጎዎች እና በአገር አቀፍ አካሎቻቸው አማካይነት ሕዝባዊ ድርጅቶች ሕግን የማመንጨት መብት አላቸው::

## አንቀጽ 73

1. ብሔራዊ ሸንጎ ከአባላቱ ከሦስት ሁለቱ እጅ ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይኖረዋል::

2. ማንኛውም አዋጅና የሸንጎው ውሳኔ ከተገኙት አባላት ከግማሽ በላይ በሆነ የድምፅ ብልጫ ሲደገፍ እንደጸደቀ ይቆጠራል:: ሆኖም በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 120 የተደነገገው እንደተጠበቀ ነው::

## አንቀጽ 74

ብሔራዊ ሸንጎ የሚያደርጋቸው ስብሰባዎች በዝግ እንዲሆኑ ካልወሰነ በስተቀር በግልጽ ይካሄዳሉ::

.../

ECLN

## አንቀጽ 75

የብሔራዊ ሸንጎ አባላት የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴዎች ናቸው።

## አንቀጽ 76

1. አንድ የሕዝብ እንደራሴ ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተገኘ በስተቀር ያለ ብሔራዊ ሸንጎ ወይም ሸንጎው ባልተሰበሰበት ጊዜ ያለ መንግሥት ምክር ቤት ፈቃድ አይያዝም፣ በወንጀልም አይከሰስም።

2. አንድ የሕዝብ እንደራሴ በሸንጎውና በሸንጎው አካላት ስብሰባዎች ላይ በሚሰጠው አስተያየት ምክንያት አይጠየቅም፣ አይከሰስም።

## አንቀጽ 77

1. የሕዝብ እንደራሴዎች በመንግሥት አካላት የወጡ ሕጎችንና የተላለፉ ውሳኔዎችን አፈፃፀም ይከታተላሉ።

2. የሕዝብ እንደራሴዎች ለመንግሥት አካላት፣ ለሕዝባዊና ለሌሎች ድርጅቶች ጥያቄ የማቅረብ መብት አላቸው፤ ተጠያቂዎቹም ተገቢውን መልስ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

## አንቀጽ 78

የሕዝብ እንደራሴዎች መደበኛ ሥራቸውን እንደያዙ ይቆያሉ። የእንደራሴነት ተግባራቸውን ለማከናወን እንዲችሉ ሊሟሉ የሚገባቸው ሁኔታዎች በሕግ ይወሰናሉ።

## አንቀጽ 79

1. እያንዳንዱ የሕዝብ እንደራሴ ለመረጠው ሕዝብ በብሔራዊ ሸንጎው የወጡ ሕጎችንና የተላለፉ ውሳኔዎችን የማብራራትና ከመረጠው ሕዝብ አስተያየትን የመቀበል፣ ለሚቀርብለት ጥያቄም ተገቢ መልስ የመስጠት ኃላፊነት አለበት።

2. እያንዳንዱ የሕዝብ እንደራሴ ለመረጠው ሕዝብ ስለሥራው እንቅስቃሴ በየወቅቱ ዘገባ ያቀርባል::

## አንቀጽ 80

አንድ የሕዝብ እንደራሴ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የሚከተለውን ቃል ይገባል:-

"ለኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ነፃነትና አንድነት ለመቆም፣ ለሶሻሊዝም ታማኝ ለመሆን፣ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም ለማስቀደም፣ ለዚህ ሕገ መንግሥትና ለሌሎችም ሕጎች ተፈፃሚነት ለመሥራት ቃል አገባለሁ::"

## አንቀጽ 81

የብሔራዊ ሸንጎን የአሠራር ሥርዓት እንደዚሁም የሕዝብ እንደራሴዎችን ጥቅማ፣ ምርጫ፣ ተጠሪነት፣ ልዩ መብት፣ ተግባርና የውክልና መሠረዝ የሚመለከቱት የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጾች በማንኛውም ደረጃ ለሚቋቋሙ ሸንጎዎችና ለሚመረጡ የሕዝብ እንደራሴዎች እንደአግባቡ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል::

## ምዕራፍ ዐሥር

## የመንግሥት ምክር ቤት

## አንቀጽ 82

1. የመንግሥት ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ መሠረት የሚቋቋም፣ የብሔራዊ ሸንጎ ቋሚ አካል ሆኖ የሚሠራ የመንግሥት ሥልጣን አካል ነው::

2. የመንግሥት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ ጸሐፊና አባላት ይኖሩታል::

3. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት የመንግ ሥት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ነው::

4. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ፕሬዚዳንት የመንግሥት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ነው::

## አንቀጽ 83

የመንግሥት ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል:-

1. ሀ. የሕገ መንግሥትንና የሌሎች ሕጎችን ተግባራዊነት ያረጋግጣል፤

   ለ. ሕገ መንግሥትንና ሌሎች ሕጎችን ይተረጉማል፤

   ሐ. በብሔራዊ ሸንጎ፣ በመንግሥት ምክር ቤትና በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ከወጡት ሕጎች ጋር የሚቃረኑ ተጠሪነታቸው ለሸንጎው የሆኑ የመንግሥት አካላት የሚያወጧቸውን ደንቦችና መመሪያዎች ይሽራል፤

   መ. ዓለም አቀፍ ውሎችን ያጸድቃል፣ ይሰርዛል፤

   ሠ. ምሕረት ያደርጋል፤

   ረ. ዜግነትን ይሰጣል፤

   ሰ. የፖለቲካ ጥገኝነትን ይሰጣል፤

   ሸ. ሜዳይ፣ ኒሻንና ሽልማት ይሰጣል::

2. ሀ. የብሔራዊ ሸንጎንና የአካባቢ ሸንጎዎችን የምርጫ ቀን ያስታውቃል፤

   ለ. የብሔራዊ ሸንጎ መደበኛና አስቸኳይ ጉባኤዎችን ይጠራል፤

   ሐ. የብሔራዊ ሸንጎ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚሽኖችን ሥራ ያስተባብራል፤

   መ. የመከላከያ ምክር ቤትን ያቋቁማል፤

   ሠ. የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ ብሔራዊ የሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴና ዋና ኦዲተር የተሰጣቸውን ኃላፊነት መወጣታቸውን ይከታተላል፤

.../

ረ. በብሔራዊ ሸንጎ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

ሰ. ስለሥራው እንቅስቃሴ ለብሔራዊ ሸንጎ ዘገባ ያቀርባል።

3. የመንግሥት ምክር ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ለማዋል ሕግ ሲያስፈልግ ድንጋጌዎችን ያወጣል።

## አንቀጽ 84

1. የመንግሥት ምክር ቤት ብሔራዊ ሸንጎ በማይሰበሰብበት ጊዜ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 120 እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ ድንጋጌዎችን ያወጣል።

2. የመንግሥት ምክር ቤት ብሔራዊ ሸንጎ በማይሰበሰብበት ጊዜ አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር፣ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታን፣ ጦርነትን ወይም ሰላምን ሊያውጅ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት የሚወጡ ልዩ ድንጋጌዎች ለሚቀጥለው የብሔራዊ ሸንጎ ስብሰባ ቀርበው መጽደቅ ይኖርባቸዋል።

## ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## የሪፑብሊኩ ፕሬዚዳንት

## አንቀጽ 85

1. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ፕሬዚዳንት በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ 4/ሀ/ መሠረት በብሔራዊ ሸንጎ ይመረጣል፤ ተጠሪነቱም ለብሔራዊ ሸንጎ ነው።

2. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ፕሬዚዳንት የሥራ ዘመን የብሔራዊ ሸንጎ የሥራ ዘመን ይሆናል።

.../

ECLN

## አንቀጽ 86

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት:-

1. ርእሰ መንግሥት ነው፤
2. ሪፐብሊኩን በውስጥና በውጭ ይወክላል፤
3. የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ነው::

## አንቀጽ 87

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባር በዚህ ሕገ መንግሥትና በሌሎች ሕጎች መሠረት ያከናውናል:-

1\. ሀ. የአገሪቱ የውስጥና የውጭ ፖሊሲ በተግባር መተርጎሙን ያረጋግጣል፤

ለ. ጠቅላይ ሚኒስትርን፤ በጠቅላይ ሚኒስትሩም አቅራቢነት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮችንና ሌሎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላትን ለብሔራዊ ሸንጎ አቅርቦ ያስመርጣል፤

ሐ. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሰጠውን ኃላፊነት መወጣቱን ያረጋግጣል፤ እንዳስፈላጊነቱም ምክር ቤቱን ይሰበስባል፤

መ. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትን፤ ምክትል ፕሬዚዳንቶችንና ዳኞችን፤ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን፤ የብሔራዊ ሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴ ሊቀመንበርንና ዋና ኦዲተርን ለብሔራዊ ሸንጎ አቅርቦ ያስመርጣል፤

ሠ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት፤ ብሔራዊ የሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴና የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የተሰጣቸውን ኃላፊነት መወጣታቸውን ያረጋግጣል::

.../

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

2\. ሀ. ዓለም አቀፍ ውሎችን ይቀቀሏል፤

ለ. ዲፕሎማቲክ ግንኙነቶችን ይመሠርታል፤ ዲፕሎማቲክ መልዕክተኞችን ይሾማል፤

ሐ. የውጭ አገር ዲፕሎማቲክ መልዕክተኞችን የሹመትና የስንብት ደብዳቤ ይቀበላል።

3\. ሀ. የመከላከያ ምክር ቤትን አባላት ይሾማል፤ ምክር ቤቱንም ይሰበስባል፤

ለ. ከፍተኛ የመንግሥት የሲቪልና የውትድርና ማዕረጎችን ይሰጣል፤

ሐ. ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ሹመት ያስታውቃል፤

መ. ይቅርታ ያደርጋል።

4\. የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት በዚህ አንቀጽ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ለማዋል ሕግ ሲያስፈልግ የፕሬዚዳንት ድንጋጌዎችን ያወጣል።

5\. ሀ. በብሔራዊ ሸንጎ፣ በመንግሥት ምክር ቤትና በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚወጡትን ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ ያውጃል፤

ለ. በብሔራዊ ሸንጎ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

ሐ. ስለሥራው እንቅስቃሴ ለብሔራዊ ሸንጎ ዘገባ ያቀርባል።

## አንቀጽ 88

1\. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ብሔራዊ ሸንጎ በማይሰበሰብበት ጊዜ አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር፡-

ሀ. ጠቅላይ ሚኒስትርን፣ በእርሱም አቅራቢነት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮችንና ሌሎች የምክር ቤት አባላትን ይሾማል፣ ይሽራል፤

ለ. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትን፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶችንና ዳኞችን፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን፣ የብሔራዊ ሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴ ሊቀመንበርንና ዋና ኦዲተርን ይሾማል፣ ይሽራል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚደረጉ ውሳኔዎች በፕሬዚዳንት ለዮ ድንጋጌ የሚታወጁ ሆነው ለሚቀጥለው የብሔራዊ ሸንጎ ስብሰባ ቀርበው መጽደቅ ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 89

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ፕሬዚዳንት ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በብሔራዊ ሸንጎ የሚከተለውን ቃል ይገባል፡—

"በዚህ ሸንጎና በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ይህን ታሪካዊ ኃላፊነት ስቀበል፤ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፤ ነፃነትና አንድነት በቁራጥነት ለመጠበቅ፤ ለሶሻሊዝም ግንባታ፤ ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ደኅንነት፤ ፍላጐትና ጥቅም መከበር፤ ለብሔረሰቦች እኩልነት መረጋገጥ በሙ ቀኝነትና ባለመ ታከት ለመሥራት፤ ለዚህ ሕገ መንግሥትና ለሌሎች የአገሪቱ ሕጐች ተገዥ ለመሆን፤ ምንጊዜም ለኢትዮጵያ ክብር፤ እድገትና ብልጽግና በታማኝነት ለማገልገል ቃል እገባለሁ፡፡"

## ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት
## የሚኒስትሮች ምክር ቤት

## አንቀጽ 90

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማለትም መስተዳድሩ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ከፍተኛ አስፈፃሚና አስተዳደራዊ አካል ነው፡፡

2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጠቅላይ ሚኒስትር፤ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች፤ ሚኒስትሮች፤ ኮሚሽነሮችና በሕግ በሚወሰነው መሠረት ሌሎች አባላት የሚገኙበት ምክር ቤት ነው፡፡

## አንቀጽ 91

1. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ 4/መ/ እና አንቀጽ 87 ንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት በብሔራዊ ሸንጎ ይመረጣሉ፡፡

ECLN

.../

2. መንግሥት ለነዚህ ነፃነቶች ተግባራዊ መሆን አስፈላጊውን ቁሳዊና ሞራላዊ ድጋፍ ይሰጣል::

## አንቀጽ 49

1. የኢትዮጵያውያን ከቦታ ወደ ቦታ የመዘዋወር ነፃነት የተረጋገጠ ነው::

2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ግዛት ውስጥ የመኖርያ ስፍራ የመለዋወጥ ነፃነት አለው::

## አንቀጽ 50

የኢትዮጵያውያን የመልዕክት ምሥጢር ነት የተረጋገጠ ነው::

## አንቀጽ 51

1. ኢትዮጵያውያን የመምረጥና የመመረጥ መብት አላቸው::

2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የአእምሮ መታወክ ከሌለበትና የመምረጥና የመመረጥ መብቱ በሕግ የተገፈፈ ካልሆነ በስተቀር የብሔረሰብ፣ የጾታ፣ የሃይማኖት፣ የሥራ ዓይነት፣ የማኅበራዊና የሌላም ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግበት 18 ዓመት ሲሞላው ለመንግሥት ሥልጣን አካላት አባላትን የመምረጥና 21 ዓመት ሲሞላው ለአባልነት የመመረጥ መብት አለው:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 52

1. ኢትዮጵያውያን የመንግሥትና የሕዝባዊ ድርጅቶችን አሠራር በሚመለከት አስተያየትና በማስረጃ የተደገፈ ሒስ የማቅረብ መብት አላቸው::

.../

ECLN



2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሥራ ዘመን የብሔራዊ ሸንጎ የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡ አዲስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት እስኪመረጥ ድረስ ያለው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሥራ ላይ ይቆያል፡፡

3. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ሸንጎ ነው፡፡ ሸንጎው በማይሰበሰብበት ጊዜ ተጠሪነቱ ለመንግሥት ምክር ቤትና ለሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 92

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮችና በሕግ በሚወሰነው መሠረት ሌሎች አባላት የሚገኙበት ቋሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 93

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡–

1. በብሔራዊ ሸንጎ፣ በመንግሥት ምክር ቤትና በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የወጡ ሕጎችና የተሰጡ ውሳኔዎች በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፤ ደንቦችን ያወጣል፤ መመሪያዎችን ይሰጣል፤

2. የሚኒስቴሮችን፣ የኮሚሽኖችንና በቀጥታ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑትን ሌሎች የመንግሥት አስተዳደር አካላት ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፤

3. የአስተዳደር አካባቢና የራስ ገዝ አካባቢ ሸንጎዎች የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎችን ሥራ ይቆጣጠራል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 የተመለከቱት አካላት ውሳኔዎች ሕግን የሚጻረሩ ሆነው ሲገኙ ይሽራል፤ እንዳስፈላጊነቱም እንዲስተካከሉ መመሪያ ይሰጣል፤

5. የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ዕቅዶችን ያዘጋጃል፤ ለብሔራዊ ሸንጎ ያቀርባል፤ ሲጸድቁም ተግባራዊነታቸውን ያረጋግጣል፤

6. ዓመታዊ በጀትን ያዘጋጃል፤ ለብሔራዊ ሸንጎ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

..../

7. ስለ ፊዴራሉ የውጭ ግንኙነት ለብሔራዊ ሸንጎ፣ ለመንግሥት ምክር ቤትና ለፊዴራሉ ፕሬዚዳንት ሒሳብ ያቀርባል። ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል።

8. መንግሥታዊ የግልግል ሥራ ያደራጃል፣ ይመራል።

9. የሀገሪቱን ጥቅም፣ የሕዝቡን ደኅንነትና የዜጎችን መብት ለማስከበርና ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል።

10. ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል።

11. ከብሔራዊ ሸንጎ፣ ከመንግሥት ምክር ቤትና ከፊዴራሉ ፕሬዚዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

12. ስለ ሥራው እንቅስቃሴ ለብሔራዊ ሸንጎና ሸንጎው በማይሰበሰብበት ጊዜ ለመንግሥት ምክር ቤትና ለፊዴራሉ ፕሬዚዳንት በየወቅቱ ዘገባ ያቀርባል።

## አንቀጽ 94

ጠቅላይ ሚኒስትር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል:-

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይሰበስባል።
2. የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይወክላል። ሥራውን ይመራል፣ ያስተባብራል።
3. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጡ ደንቦችና የተሰጡ ውሳኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።
4. ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮችንና ሌሎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላትን በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 87 ንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ መሠረት ለማስመረጥ ለፊዴራሉ ፕሬዚዳንት ያቀርባል።
5. በመንግሥት ምክር ቤትና በፊዴራሉ ፕሬዚዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀጽ 95

የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት በወል ለሚወሰዱት እርምጃ የጋራ፣ በተናጠል ለሚወስዱት እርምጃ የግል ኃላፊነት አለባቸው።

ECLN

## ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

## የአስተዳደር አካባቢና የራስ ገዝ አካባቢ

## የሥልጣንና የአስተዳደር አካላት

### አንቀጽ 96

የአስተዳደር አካባቢና የራስ ገዝ አካባቢ ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን አካል የአካባቢው ሸንጎ ነው።

### አንቀጽ 97

1. የአካባቢ ሸንጎዎች የሥራ ዘመን በሕግ ይወሰናል።
2. የሸንጎዎቹ የስብሰባ ጊዜ በሕግ ይወሰናል።

### አንቀጽ 98

የአስተዳደር አካባቢና የራስ ገዝ አካባቢ ሸንጎ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

1. የመንግሥት ሕጎች፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
2. ለበታች ሸንጎዎች መመሪያ ይሰጣል፤ ሥራቸውን ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤
3. የአካባቢውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕቅዶችና በጀት ይወሰናል፤ በብሔራዊ ሸንጎ ሲጸድቁም በሥራ ላይ ያውላል፤
4. በሥልጣኑ ክልል ውስጥ የሚገኙ የሥራ እንቅስቃሴዎችን የሚመለከቱ መመሪያዎች ይሰጣል፤
5. የአካባቢውን ፍርድ ቤት ዳኞች ይመርጣል፤
6. ከአባላቱ መካከል የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይመርጣል፤ ሥራውንም ይቆጣጠራል፤
7. ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚሽኖች ያቋቁማል፤

…/

8. ስለአካባቢው የሥራ እንቅስቃሴ ለሚቀጥለው የበላይ ሸንጎ ዘገባ ያቀርባል::

## አንቀጽ 99

የአስተዳደር አካባቢና የራስ ገዝ አካባቢ ሸንጎ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ:—

1. የበላይ አካላት ሕጎች፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳል።

2. በአካባቢው ውስጥ የሚገኙት የበላይ የመንግሥት አካላት የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች ይከታተላል።

3. የበታች ሸንጎዎች ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎችን ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል።

4. በአካባቢው ሥልጣን ክልል ውስጥ የሚገኙት የአስተዳደር፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል ድርጅቶችን ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል።

5. የአካባቢውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እቅዶችና በጀት ያዘጋጃል። ከጸደቀም በኋላ በሥራ ላይ ያውላል።

6. በበላይ አካላት የሚሰጡትን ሌሎችንም ተግባሮች ያከናውናል።

7. ለአካባቢው ሸንጎና ለበላይ አስፈፃሚ አካል በየወቅቱ ዘገባ ያቀርባል::

## አንቀጽ 100

የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 98 እንደተጠበቀ ሆኖ የራስ ገዝ አካባቢ ሸንጎዎች የሚኖራቸው የተለየ ሥልጣንና ተግባር በብሔራዊ ሸንጎ ይወሰናል::

ECLN

## ምዕራፍ ዐሥራ አራት

## ዳኝነት

### አንቀጽ 101

1. በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዳኝነት ሥልጣን የአንድ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የአስተዳደር አካባቢያዎችና የራስ ገዝ አካባቢያዎች ፍርድ ቤቶችና የሌሎችም በሕግ የሚቋቋሙ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

2. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፍርድ ቤቶች በሕግ የተረጋገጡ የመንግሥትና የሕዝባዊ ድርጅቶችን፣ የሌሎች ማኅበራትንና የግለሰቦችን መብቶች፣ ጥቅሞችና ነፃነቶች ያስከብራሉ።

### አንቀጽ 102

1. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የሚመረጡት በብሔራዊ ሸንጎ ነው፣ የአካባቢ ፍርድ ቤቶች ዳኞች በየአካባቢያቸው ሸንጎዎች ይመረጣሉ።

2. የዳኞች የሥራ ዘመን የመረጣቸው ሸንጎ የሥራ ዘመን ይሆናል።

3. የመረጣቸው ሸንጎ ዳኞችን ከሥራቸው እንዲነሱ ሊያደርግ ይችላል።

4. የዳኞች ጥቆማ፣ ምርጫና አስተዳደር በሕግ ይወሰናል።

### አንቀጽ 103

1. በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የበላይ የዳኝነት አካል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው።

2. ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአገሪቱ ፍርድ ቤቶች ሁሉ የሚካሄዱ የዳኝነት ተግባሮችን የመቆጣጠር ሥልጣን አለው።

ECLN

.../

## አንቀጽ 104

ከሕዝቡ የሚመረጡ አማኝ ዳኞች በፍርድ ቤቶች በዳኝነት ይሠራሉ። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 105

ዳኞችና አማኝ ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ፤ ከሕግ በስተቀር በማንኛውም ሌላ ሥልጣን አይመሩም።

## አንቀጽ 106

ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ተግባራቸውን የሚያከናውኑበትን ቋንቋ ለማይችል ባለጉዳይ የትርጉም አገልግሎት ይሰጣሉ።

## አንቀጽ 107

በዝግ ችሎት እንዲታይ በሕግ የተወሰኑ ምክንያቶች ካላጋጠሙ በስተቀር ማንኛውም ጉዳይ የሚታየው በግልጽ ችሎት ይሆናል።

## አንቀጽ 108

ፍርድ ቤቶች ሥራቸውን በሚመለከት ለመረጡዋቸው ሸንጎዎች በየወቅቱ ዘገባ ያቀርባሉ።

.../

http://www.ethcriminalawnetwork.com/

ECLN



## ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

## የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት

### አንቀጽ 109

1. የመንግሥት አካላት፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት፣ ባለሥልጣኖቻቸውና ማንኛውም ግለሰብ ሕግን ማክበራቸውንና የሕጉንም አንድ ወጥ አፈጻጸም የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ያረጋግጣል::

2. የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይመራል::

### አንቀጽ 110

1. ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በብሔራዊ ሸንጎ ይመረጣል፤ ተጠሪነቱም ለብሔራዊ ሸንጎ ነው:: ሸንጎው በማይሰበሰብበት ጊዜ ተጠሪነቱ ለመንግሥት ምክር ቤትና ለሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ይሆናል::

2. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሥራ ዘመን የብሔራዊ ሸንጎ የሥራ ዘመን ይሆናል::

### አንቀጽ 111

በሁሉም ደረጃ የሚገኙ ዐቃብያነ ሕግ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይሾማሉ፤ ተጠሪነታቸውም ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይሆናል::

### አንቀጽ 112

ዐቃብያነ ሕግ ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በስተቀር በአካባቢ የመንግሥት አካላት አይመሩም::

### አንቀጽ 113

የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት አደረጃጀት፣ አሠራርና አስተዳደር በሕግ ይወሰናል::

.../

# ክፍል አራት

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

## ሰንደቅ ዓላማ፣ አርማ፣ መዝሙር፣ ቋንቋና ርእሰ ከተማ

### አንቀጽ 114

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሀሉ ቢጫና ከታች ቀይ ቀለም ያለው ባለ አግድም ቀርጽ ነው:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

### አንቀጽ 115

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አርማ በሕግ ይወሰናል::

### አንቀጽ 116

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ብሔራዊ መዝሙር ይኖረዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

### አንቀጽ 117

የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የመንግሥት የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው::

### አንቀጽ 118

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ርእሰ ከተማ አዲስ አበባ ናት::

ECLN

## ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት

## የሕገ መንግሥት ሕጋዊ ኃይልና መሻሻል

### አንቀጽ 119

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት የአገሪቱ የበላይ ሕግ ነው:: ማንኛውም ሕግና ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

### አንቀጽ 120

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት የብሔራዊ ሸንጎ አባላት ከአራት ሦስቱ እጅ በሚደግፉት ውሳኔ ብቻ ሊሻሻል ይችላል::

ECLN